የኢትዮጵያ ልማት ባንክ

# ዲጂታል ዜና መጽሔት

ቁጥር 1 ሚያዚያ 2015 ዓ.ም

## የአራተኛው ዙር የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች ሥልጠና የመጀመሪያ ምዕራፍ በስኬት ተጠናቀቀ




**የኢትዮጵያ ልማት ባንክ** የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾችን አቅም ለመገንባት ከየካቲት 14 -18 ቀን 2015 ለአምስት ተከታታይ ቀናት በ57 ከተሞች በ95 ማእከላት ሲያካሂድ የነበረው ሥልጠና በስኬት ተጠናቀቀ።

ባንኩ ከጥር 6 እስከ 21 ቀን 2015 ዓ.ም በነበረው የምዝገባ ጊዜ እጅግ በርካታ ወጣቶች ለስልጠናው ለመሳተፍ በሁሉም የባንኩ ቅርንጫፎች በስፋት ተንቀሳቅሰው እንደነበር የሚታወስ ሲሆን፣ በአጠቃላይም 435 ሺሕ አንቀሳቃሶች መመዝገባቸው ተረጋግጧል። ይህንን በማስመልከት በሥልጠናው መክፈቻ ንግግር ያደረጉት የባንኩ ፕሬዝዳንት ዶክተር ዮሐንስ አያሌው <<በዚህ ሥልጠና ለመሳተፍ የተመዘገቡት በአጠቃላይ 435 ሺህ ሲሆኑ፣ ይህንን ተመዝጋቢ ከአሰልጣኝ ቁጥር፣ ከሎጂስቲክስና ከፋሲሊቲ አንጻር፣ በአንድ ዙር ለማስተናገድ የሚቻል አልሆነም። በመሆኑም ሠልጣኞች በተመዘገቡበት ማዕከል ባመዘጋገባቸው ቅደም ተከተል መሠረት ሥልጠናውን በ3 ምዕራፍ ለመስጠት ወስነናል።>> ብለው ነበር።

በዚህም መሠረት ባንኩ የመጀመሪያውን ምዕራፍ ከየካቲት 14-18 ቀን 2015 በሰጠበት ሥልጠና መርሐ ግብር 111,408 ሺህ ተመዝጋቢዎች እንደተመዘገቡበት ቀን ቅደም ተከተል ተለይተው እንዲሠለጥኑ በመወሰኑ ትግራይን ጨምሮ በመላው ሀገሪቱ ባሉ ሁሉም ክልሎች በተለያዩ ሥልጠና ማእከላት ለሥልጠናው ተደልድለዋል። ሥልጠናውም በስኬት ተካሂዷል። በሥልጠናውም በየማእከላቱ ከተደለደሉት መካከል በአማካኝ 89,099 ያህል ሠልጣኞች በሥልጠናው ታድመዋል። ይህ ማለት እንዲሠለጥኑ ከተመደቡት መካከል ከ89 በመቶ በላይ ሠልጣኞች ተካፍለዋል።

የባንኩ ፕሬዝዳንት ዶክተር ዮሐንስ አያሌው 4ኛውን ዙር ሥልጠና ልዩ ስለሚያደርጉት ጉዳዮች ሲያነሡ <<በዚህ ስልጠና ከ435 ሺህ በላይ የሆኑ ሠልጣኞች የተመዘገቡበት ሲሆን ፣ ከዚህ በፊት ተደራሽ ያልነበሩ እንደ ጎዴና ጂንካ የመሳሰሉ ከተሞች በዚህ በ4ኛው ዙር የመጀመርይ ምዕራፍ ሥልጠና እንዲካተቱ የተደረገበት ነው። ይህም ሥልጠናውን ፍትሐዊ ለማድረግ እየተሄደበት ያለውን ርቀት የሚያመላክት ነው። በተጨማሪም የትግራይ ክልል ወጣቶች በዚህ ሥልጠና እንዲካተቱ መደረጉ ሥልጠናውን ልዩ ያደርገዋል።>> ብለዋል።

ከመጀመሪያ ዙር እስከ ሦስተኛ የሥልጠና ዙር ተካሂዶባቸው በማያውቁ ከተሞች ማለትም ደብረ ብርሃን፣ አሳይታ፣ መቱ፣ አክሱም፣ ሽረ፣ ወልዲያ፣ መካነሰላም፣ ሁመራ፣ ሞጣ፣ ጎዴ፣ ፍኖተ ሰላም፣ ፍቼ፣ ቦንጋ፣ ወልቂጤ፣ ጂንካ፣ መተከል፣እንጅባራ፣ ሚዛን፣ ኮምቦልቻ፣ ሰቆጣ፣ ደባርቅ፣ ዲላ፣ ይርጋለም፣ ዳንሻ፣ በደሌ፣ አላማጣ፣ ማይጨወ፣ ደምቢዶሎ፣ ጊምቢ፣ አምቦ፣ ሆሳዕና፣ ሳውላ፣ ወሊሶ .... . ሥልጠና ተሰጥቷል። ይህም ባንኩ አገልግሎቱን ወደ ደንበኞቹ ለማቅረብና ለማስፋት የያዘው ሪፎርም ሥራ አካል ሆኖ የሚታይ ነው።

ሥልጠናው በርካታ ተሳታፊዎች የተስተናገዱበት ሰፊ ሀገር አቀፍ ሥልጠና ቢሆንም ያለምንም እንከን በሰላምና በስኬት ተጠናቋል። ሥልጠናው ስኬታማ እንዲሆን የዓለም ባንክ፣ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር፣ ሀገራችን ዩንቨርሲቲዎች በተባባሪና ደጋፊነት የተወጡት ሚናም ከፍተኛ ግምት ተሰጥቶታል።

በሥልጠናው መክፈቻ አዲስ አበባ አስተዳደር ከንቲባ ክብርት ወ/ሮ አዳነች አቤቤ፣ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት አቶ ሺመልስ አብዲሳ፣ የደቡብ ምዕራብ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዝዳንት ዶ/ር ነጋሽ ዋጌሾ በክብር እንግድነት በመገኘትና የመክፈቻ ንግግር በማድረግ ተሳትፈዋል።

ለሥልጠናው ለመሳተፍኑ ጥሪ ከተደረገላቸው 112 ሺህ ሠልጣኞች ሲሆኑ፣ ከእነዚህም መካከል ተጣርቶ በባንኩ መስፈርት መሠረት በብቃት በሥልጠናው ተሳታፊ ለነበሩ የምስክር ወረቀት እንደሚዘጋጅላቸው ታውቋል።

# በ4ኛ ዙር የኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች ሥልጠናላይ የተሳተፉ የመንግስት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች መልዕክት በከፊል




ወ/ሮ አዳነች አቤቤ - የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ

ባንኩ የሚሰጠው የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዝ አንቀሳቃሾች ሥልጠና ከዚህ ቀደም የወሰዱ ሰዎች የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ባቀረበላቸው የሊዝ ፋይናንስ ድጋፍ ወደ ሥራ ገብተው ያመጡትን ተጨባጭ ለውጥ በባንኩ ሚዲያና በሌሎች የሚዲያ አማራጮች ተመልክተናል። ከዚህ አንጻር ይህ በኢትዮጵያ ልማት ባንክ የቀረበው ሥልጠና ከከተማችን የጥቃቅንና አነስተኛ ስትራተጂ ጋር የሚጣጣም በመሆኑ ወደ ሥራ ለሚገቡት ብቻ ሳይሆን በተለይ በዚህ አደረጃጀት ተደራጅተው ወደ ሥራ ለገቡ ኢንተርፕራይዞች የሚስተዋልባቸውን የእውቀትና የክህሎት ክፍተት በመሙላት በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ቀጣይ የእድገት ደረጃ በመሸጋገር ለውጥ እንዲያመጡ የሚረዳ ነው።

የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች በዚህ ስልጠና ከታገዙ የአገራችንን የስራ አጥነት ችግር ከማቃለል ባለፈ፣ በመንግስት ቅድሚያ ትኩረት በተሰጣቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች፣ በተለይም በግብርናና በከተማ ግብርና ልማት በመሰማራት የምግብ ዋስትናችንን ለማረጋገጥ ያስችሉናል።

አዲስ አበባ ከተማችን የአፍሪካ የፖለቲካ መናኸሪያ ከመሆን ባለፈ ከዓለም የዲፕሎማሲ ከተሞች መካከል የምትመደብ ነች። ከዚህ ጋር በተያያዘ በከተማችን የሚኖረው የቢዝነስና የሥራ ዘርፎች እጅግ በርካታ በመሆናቸው ሰልጣኞች የሚፈልጉትን ስራ በመንግስት ከተቀመጡት የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር አጣጥመው ለመስራት የተሻለ እድል ይሰጣቸዋል። በመሆኑም የከተማችን ሰልጣኞች የሚጠብቃችሁን በርካታ የስራ እድል ግምት ውስጥ በማካተት ስልጠናውን በከፍተኛ ንቃት እንድትከታተሉ አደራ እላለሁ።

ይህ ስልጠና የከተማ አስተዳደራችን በልማት ዘርፍ የሚሰራውን ተግባር የሚደግፍና የሚያጠናክር በመሆኑ ወደ ስራ የሚገቡትን በመደገፍ፣ የመስሪያ ቦታ በማመቻቸት፣ በአጠቃላይ እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሚጠበቅብንን ሁሉ ለመወጣት ዝግጁ መሆናችንን በከተማ አስተዳደሩ ስም ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።



አቶ ሽመልስ አብዲሳ - የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፕሬዝዳንት

ሥራ ፈጣሪዎች (ኢንተርፕርነሮች) የሌሉበት ኢኮኖሚ አይባዛም። ያልተባዛ ኢኮኖሚ ደግሞ በቂ የሥራ ዕድል መፍጠር አይችልም። ጫናዎችን መቋቋም አይችልም። አስፈላጊውን ጥቅም ለሀገር ሕዝብ ሊያመጣ አይችልም። ስለዚህ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በሚፈለገው ደረጃ እንዲለማ ከተፈለገ ዋነኛው መፍትሔ የሥራ ፈጠራ ጉዳይ ነው። ኢንትርፕርነርሸፕን ለማምጣት ደግሞ ሥልጠና በማዘገጀት አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠት መሥራት ያስፈልጋል፡፡ በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከሌሎች ባንኮች በተለየ ትኩረት ሰጥቶ ባለፉት ሦስት ዓመታት አስደናቂ ሥራ ሠርቷል። በዚሁ አጋጣሚ በኦሮምያ ክልል መንግሥት ስም ይህን የሥልጠና ዕድል ባገኛችሁ ሠልጣኞች ስም ባንኩን ማመስገን እፈልጋለሁ፡፡ ሌሎች ባንኮች አርአያውን ሊከተሉት ይገባል። ሊማሩበት የሚገባ ነው። ባንኮች አነስተኛ ቢዝነሶች ላይም ትኩረት አድርገው ቢሠሩ ኢትዮጵያ ያላትን አቅም አሟጦ መጠቀም ይቻላል፡፡ ኢትዮጵያ ብዙ አቅም እንዳላት እናወራለን፤ ይህ ግን ወደ አቅም ሊቀየር የሚችለው እውነተኛኢንተርፕርነሮች ሲኖሩ ብቻ ነው። እውነተኛ ኢንተርፕርነሮች እንዲፈጠሩ ካደረግን፣ ዕድል ከሰጠናቸው ከደገፍናቸው ኢኮኖሚውን እንዲያባዙት አሟልተው እንዲጠቀሙበት ካደረግን ከውጪ የሚገባውንም በሀገር ውስጥ ማምረት እንችላለን። ሀገር ውስጥ የለንን ምርት በከፍተኛ ደረጃ ልንጠቀምብት እንችላለን። ይህን በማድረግ በእጃችን ያለንን እምቅ አቅም ወደ ተጫባጭ መቀየር ይቻላል።

በዚህም ሁሉም የባንኩ ቤተሰቦች መመስገን አለባቸው። አብዛኞቹ የፋይናንስ ተቋማት ትልልቅ አቅም ላላቸው እንጂ አነስተኞቹ ላይ ሲያተኩሩ አይታይም። በኦሮምያ መንግሥት ስም ቃል የምገባው እነዚህን ሠልጣኞች በተቻለን መጠን ወደ ሥራ ለማስገባት እንደምን ቀሳቀስ ነው።



ዶ/ር ነጋሽ ዋጌሾ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክትል ፕሬዝዳንት

እንደ አገርም ሆነ በክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የሚኖራቸውን ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳ ስንመለከት ደግሞ በተፈጥሮ የታደልነውን ገጸ በረከት እንዲሁም ያለንን እምቅ የሰው ጉልበትና የስራ ፍላጎት አስተባብረን በተጠናና በዕውቀት ላይ በተመሰረቱ የቢዝነስ አማራጮች ብንሰማራ የምናስበውን እድገት እውን ማድረግ እና የዜጎቻን ሕይወት መለወጥ እንደምንችል የኢትዮድያ ልማት ባንክ የያዘው መንገድ ማሳያ ነው።

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ምንም እንኳ በቅርብ ዓመታት የተመሰረተ ክልል ይሁን እንጅ በተለይም በተፈጥሮ ገጸ በረከቱ በተለይም በቡናው ዘርፍ፣በቅመማ ቅመም ዘርፍ፣በደን ልማት ዘርፍ፣በፍራፍሬና በሻይ ልማት ዘርፍ ፣ በእንስሳት እርባታና በቱሪዝም ዘርፎች ያለውን ያልተነካ አቅም አልምቶ ሥራ ላይ ለማዋልና የክልላችን ፣ ብሎም የአገራችንን ህዝቦች ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ይህ የአራተኛው ዙር የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ስልጠና አስፈላጊ እንደሆነ ያምናል።

ይህ በዓይነቱ ልዩ የሆነና ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሰልጣኝ የሚሳተፍበት እንደመሆኑ እጅግ ከፍኛ ሀብት እና የዝግጅት ጊዜ ወጥቶበት በኢትዮጵያ ልማት ባንክ የተዘጋጀላችሁ ስልጠና በየክልላችሁና በየአካባቢያችሁ ያለውን የስራ እድልና እና በአቅራቢያችሁ የሚገኘውን የተፈጥሮ በረከት ትርጉም ሰጥታችሁ እንድትመለከቱና በአግባቡ እንድትጠቀሙ እውቀትና ክህሎት የሚያስጨብጣችሁ ስልጠና ነው። በዚህም ባልሰለጠነና በእውቀት ላይ ባልተመሰረተ የስራ አማራጭ እንዲሁም በገበያ አለመረጋጋት ሳቢያ በሚስተዋለው የዋጋ መናር ሳቢያ ኑሮ ከባድ ለሆነባቸው እንዲሁም ፍላጎት እያላቸው የስራ አማራጭ ላላገኙ ዜጎቻችን የስራ እድል ከመፍጠር በዘለለ በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ በስፋት በመግባት የምርት አቅርቦትን በማሳደግና የቴክኖሎጅ ሽግግርን መፍጠር ከእናንተ ከሰልጣኞች ይጠበቃል። ይህ ሲሆን ባለፉት ጊዜያት እንደዚህ ያሉ አማራጮችን ባለማግኜት በልምላሜ፣ በተፈጥሮ የስነ ምህዳር ሀብቱ ፣ያሉት ለስራ ምቹ የሆኑ ገጸ በርከቶች ወደ ሀብት መቀየር ሳይቻል በመቅረቱ ምክንያት አዲሱ ክልላችን በሚፈለገው ደረጃ ማደግ አልቻለም። ክልላችን ያለውን የተፈጥሮ በረከት ያክል ሳይለማ ቆይቷል በሚል ከመቆጨት በዘለለ ወደ ተግባር በመግባትና ይህንን መሰሉን እድል እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም ተባብረን ልናሳድገው ይገባል።




ወ/ሮ ሙፈሪሃት ካሚል የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ሚንስትር

አነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ጉዳይ ላይ ስንነጋገር ብዙ ጊዜ መሄጃ ያጡ ሰዎች የሚያርፉባቸው ተደርገው ይወሰዳሉ፤ በአስተሳሳብ እንደዚያ ይቆጠራሉ። ቤተሰብ፣ ተስፋ የሚያደረጉ ተቋማት ደጋፊ አይደሉም። ምን ያድርግ ልጄ ከቤት ከምትውል (ከሚውል) እስቲ ይሞክር የሚል አስተሳሳብ የሚፈትነው ዘርፍ ነው። እንደዚህ ዓይነት የተዛቡ አመለካከቶችን ከራስ ጀምሮ መታገል ይጠይቃል። ለዚህም ነው ልማት ባንክ እናንተን ሠልጣኞችን እውቀት መር ወደ ሆነ የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ ትገቡ ዘንድ ከባለድርሻ አካለት ጋር ተባብሮና ተቀናጅቶ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ እየሠራ ያለው። እናንተ አማራጭ አጥታችሁ ራሳችሁን ያዘጋጃችሁ ሳትሆኑ ኢኮኖሚውን መሠረት የምትገነቡ፣ መሠረቱን የምታረጋግጡ አርበኞች መሆናችሁን መረዳት ብቻ ሳይሆን ማማን ይጠይቃል። ባንኩ እያደረገ ያለው የፋና ወጊነት እንቅስቃሴ ከዚህ እምነት የመነጨ ነው። የነበሩትን ችግሮች ፈትቶ በስኬት ጎዳና መረማማድ ሲጀምር እንደ ሀገር የጀመርነውን ሁለንተናዊ የብልጽግና ጉዞ በማሳካት ረገድ ትልቅ ትርጉም ያለው ነው። በእኛ በኩል ባንኩ ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በበርካታ ዘርፎች አብሮ ለመሥራት የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርመን እየሄድን ነው ያለነው። አንድ ሀገር የቅድሚያ ቅድሚያ በሰጠናቸው የግብርና፣ ኢንዱስትሪ፣ የቱሪዝም የማዕድን ሥራዎች ላይ የሰው ኃይል አቅም ግንባታ ተግባራት ላይ ቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ እንደዚሁም በዘርፉ የሚታዩ ማነቆዎችን መፍታት ላይ አብረን የምንሠራቸው በርካታ ተግባራት አሉን። እስከ አሁን ድረስም ስኬታማ እንቅስቃሴ እያደረግን ካለናቸው አካላት አንዱ ልማት ባንክ ነው።

ስለዚህ አስቀድሜ እንደገለጽኩት ሠልጣኞች የእናንት ተልእኮ የዕለት ጉርስ የማግኘት ተልእኮ አይደለም፤ ከዕለት ጉርስ በላይ ሀብት መፍጠር ላይ የተመሠረተ ተልእኮ ነው። እናንተ ተልእክ የራሳችሁን ከማቆም ባለፈ ለቤተሰባችሁም የሚተርፍ ለማሕበረሰብ የሚበቃ ሀገርን የሚያጸና ተልእኮ ነው። ይህንን ተልእኮ ከዳር ከማድረስ አንጻር የመጀመሪያና ወሳኙ እናንተ ናችሁ። እናንተ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ለመጋፈጥ ወስናችሁ የጸናችሁ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ወደ መልካም ዕድል ለመለወት የወሰናችሁ የመኖርና የማኖር ዕድል ያላችሁ ናችሁ።

# የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ማኔጅመንት አባላት እና ሠራተኞች ዓለም አቀፉን የሴቶች ቀን በደማቅ ሁኔታ አከበሩ።









የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ማኔጅመንት አባላትና ሠራተኞችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ 112ኛ ጊዜ በሀገራችን ደግሞ ለ47ኛ ጊዜ የሚከበረውን የማርች 8 የሴቶች ቀን የባንኩ ፕሬዝዳንትና የልማት ባንክ ሠራተኞች ማኅበር ሊቀመንበር በተገኙበት በድምቀት ተከብሯል። የዘንድሮ በዓል በዓለም አቀፍ ደረጃ <<DigitALL:Innovation and Technology for Gender Equality>> በሚል ዋና መሪ ሐሳብ የተከበረ ሲሆን፣ በሀገራችንም ''እኔ የእኅቴ ጠባቂ ነኝ" በሚል መሪ ሐሳብ በዓሉ ተከብሯል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በድምቀት ባከብረው በዚህ በዓል የተገኙት የባንኩ ፕሬዝዳንት ዶክተር ዮሐንስ አያሌው ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከደንበኞች አንጻርና ከራሱ ሠራተኞች አንጻር የሴቶችን አቅምና ተሳትፎን ለማሳደግ እየሠራ ስላለው ሥራ አብራርተዋል። ፕሬዝዳንቱ እየተደረገ ስላለው የማብቃት ሥራ ሲያብራሩ <<በኢትዮጵያ እድገት ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎና ሁለተናዊ የኢኮኖሚ አቅም ማጎልበት እንዳለበት በመታመኑ ሴቶችን በኢኮኖሚ ለማብቃት የፋይናንስ ውሳኔ ሰጪነታቸውን ማሳደግ ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም። የኢትዮጵያ ልማት ባንክም በሀገር አቀፍ ደረጃ የሴቶችን አቅም በማሳደግ ልማት የሚኖረውን ፋይዳ በመረዳት እየሠራ ይገኛል።>> ያሉ ሲሆን፣ የባንኩን ሴት ሠራተኞች ከማብቃት አንጻር ስለተሠራው ሲገልጹም <<ባለፉት ሁለት ዓመታት የሪፎርም ሥራዎችን በመሥራት ባንካችንን ወደ ጤናማ መስመር ለማምጣት የሚያስችሉ ጥረቶችን ስናደርግ ቆይተናል። በዚህም በተያዘው በጀት ዓመት ሁለተኛ ሩብ ዓመት መጨረሻ በስራቸው፣በልምዳቸው፣ በሥራ ባሕርያቸው፣ እንዲሁም ለተቋማቸው ባላቸው መልካም ጥረት እየታዩ በተለያዩ ደረጃዎች ለሚገኙ የኃላፊነት ቦታዎች በሴቶች እንዲመሩ ምደባ አካሂደናል። በዚህ ምደባ 104 የሚሆኑ ሴት እህቶቻችን የአመራር ሰጪነት በሚጠይቀው የኃላፊነት ቦታ የተመደቡ ሲሆን፣ ይህም 20 በመቶ ያህሉ የአመራር ሰጪነት ቦታ በሴቶች እንዲመራ አድርገናል።>> ብለዋል።

በዕለቱ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የሠራተኞች መሠረታዊ ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ ዮሴፍ ተስፋዬ፣ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የሠራተኞች መሠረታዊ ማህበር የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ኃላፊ ወይዘሮ ዓለም ስዩም እና የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የባንኪንግና ፋይናንስ ምክትል ፕሬዚዳንት ወይዘሮ የምሥራች ዓለምነህ መልእክት አስተላልፈዋል። በዓሉን ለማድመቅ ሥነጽሑፍ ዝግጅቶች፣ የማነቃቂያ ንግግሮች፣ ከመደረጋቸውም ባሻገር የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዝዳንት በባንኩ የሚገኙ ሴት ሠራተኞችን በማብቃት ረገድ ለነበራቸው ሚና የዕውቅና ምስጋና ሽልማትም ተበርክቶላቸዋል።

# ልማት ባንክ የግብርና ሜካናይዜሽንን ለማስፋፋት እየሠራ ነው።




የኢትዮጵያ ልማት ባንክ የሀገሪቱን የግብርና ሜካናይዜሽን ለማስፋፋት ከፍተኛ አገልግሎት እየሰጠ ነው። ባንኩ በተያዘው በጀት ዓመት እስከ መጋቢት ወር መጀመሪያ ድረስ (በግዢ ሂደት ላይ ያሉትን ሳይጨምር) 303 ዋና ዋና የግብርና ማሽነሪዎችን ለደንበኞች ያስተላላፈ ሲሆን፣ 200ዎቹ ትራክተሮች እና 86ቱ ኮምባይነሮች ናቸው፤ ፤ ሌሎች ከእነዚህ ማሽነሪዎች ጋር አብረው የሚሠሩ ማረሻዎች፣ መከስከሻዎች፣ ማለስለሻዎች የመሳሰሉ ለግብርናው መዘመን የሚጠቅሙ ተያያዥ መሣሪያዎችም አብረው ተሠራጭተዋል። የአማራ፣ ኦሮምያ፣ የደቡብ፣ የደቡብ ምዕራብ፣ ሶማሌ፣ ጋምቤላ ክልሎች ውስጥ የሚገኙ ደንበኞች ማሽነሪዎችን መረከብ ሲጀምሩ በሌሎች ክልሎች የሚገኙ ደንበኞች የሚረከቧቸውም በግዢ ሂደት ላይ መሆናቸው ታውቋል። ደንበኞች ማሽነሪዎቹን በማቅረብ የግብርና ዘርፉን ከማልማት አንጻር ሚናውን እየተወጣ ነው።



# የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለሀገር ባለውለታዎች ቃል የገባላቸውን ድጋፍ ተቀበሉ








የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በ2015 ዓ.ም የገና በዓልን አስመልክቶ ባዘጋጀው የበዓል ልዩ ዝግጅት ላይ ለ7 የሀገር ባለውለታዎች ድጋፍ ለማድረግ ቃል በገባው መሠረት የባጃጅ ስጦታ እንዲሰጣቸው የተወሰነላቸው የካራማራው ጀግና ሻለቃ ባሻ አሊበርኬና በቦክስ ውድድር ቀዳሚው የኦሎምፒክ ተሳታፊ የነበሩት አቶ በቀለ ዓለሙ(ጋንቹ) ባጃቾቻቸውን ተረክበዋል። ባጃጆቹ በበዓሉ ዕለት ተገዝተው የቀረቡ ቢሆንም የባንኩ ባለሙያዎችና ሥራ ኃላፊዎች በቡራዩ ክፍለ ከተማ እና በለገጣፎ ክፍል ከተማ በመገኘት ማለቅ ያላባቸውን የሕግ ሂደቶች ጨርሰውና የበር ገጠማ ሥራዎች ከተከናወኑ በኋላ ለሀገር ባለውለታዎቹ ከመቶ ሺህ ብር ጋር ባጃጆችን አስረክበዋል። ባጃጃቸው ሕጋዊ ሆነው ወደ ሥራ እንዲገቡ የማድረጉን ሂደት የባንኩ ባለሙያዎች አስፈጽመዋል። ሌሎች የህክምና ድጋፍ እንዲደረግላቸው የተወሰነላቸው ባለውለታዎች (ጋዜጠኛ አስካለ ተስፋዬ፣ አርቲስት ሰሚራ አብዱራህማን፣ አርቲስት ግርማ ብስራት እና የዓለምብርሃን አበበ) በባንክ ሒሳብ ቁጥራቸው ገንዘቡ እንዲገባላቸው ተደርጓል። ቤት እንዲገዛላቸው የተወሰነላቸው አቶ አሸብር ካብታሙ ደግሞ በአዲስ አባበ አስተዳዳር በኩል ባንኩ በግዢ ቤቱን ተረክቦ ሊያስረክባቸው የጀመረው ሂደት እስከሚሳካ ለቤት ኪራይ የሚያወጡትን ወጪ ባንኩ እየሸፈነላቸው ይገኛል፡ ፡ በአጠቃላይ ባንኩ ለነዚህ የሀገር ባለውለታዎች የ 6,635,600 ብር ድጋፍ አድርጓል።



# የባንኩ ሠራተኞች ለችግረኞች ድጋፍ አደረጉ

ለችግረኞች ደጋፍ ለማድረግ የተሰባሰቡ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ማኔጅመንት አባላትና ሠራተኞች ለሁለት በጎ አድራጊ ድርጅቶችና ከተለያዩ ቦታዎች ተፈናቅለው በመጠለያ ለሚገኙ ዜጎች ሚያዝያ 4 ቀን 2015 ዓ.ም በገንዘብና በዓይነት እርዳታ አደረጉ።

የባንኩ ሠራተኞች ድጋፍ ያደረጉላቸው ድርጅቶች ጌርጌሴኖን የአዕምሮ ሕሙማን መርጃና ማገገሚያ ማዕከል እና ነህምያ ኦቲዝም ማዕከል ሲሆኑ፣ ለእያንዳንዳቸው 100 ሺህ ብር ድጋፍ አድርገዋል። ከዚህ ባሻገር ከተለያዩ ሀገራትን ክልሎች ተፈናቅለው ደብረ ብርሃን ለተሰባሰቡ ችግረኞች ለዕለት ምግብ የሚያገለግሉ በዓይነት ልዩ ልዩ ምርቶችን 100 ሺህ ብር በማውጣት ድጋፍ አድርገዋል።




የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ችግረኛ መርጃ ማኅበሩ በታህሳስ 2005 ዓ.ም ደጋፍ ማድረግ የጀመረ ሲሆን፣ እስከ 2012 ዓ.ም የትምህርት ዘመን ድረስ የልቤ ፋና አንደኛ ደረጃ ት/ቤትን በመመረጥ በችግር ምክንያት ትምህርታቸውን በአግባቡ መከታተል ያቃታቸውን ህጻናት ተማሪዎች በግቢው ውስጥ በሚገኝ የመመገቢያ ካፍቴሪያ ሙሉ የቁርስ እና የምሳ ወጪያቸውን በመሸፈን እንዲመገቡ በማድረግ፤ በትምህርት ቁሳቁስ ማለትም ዩኒፎርም፣ ቦርሳ፣ ጫማ፣ ደብተር እና እስክሪቢቶ እንዲሁም ተማሪዎቹ በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ የክትትል ሥራን በመሥራት እገዛ ሲያደርግ ቆይቷል። በተጨማሪም 100 ሺሕ በማውጣት የመጀመሪያ ዙር ድጋፍ አንገብጋቢ የሆነ እርዳታ ለሚያስፈልገው ለኢትዮጵያ የልብ ሕሙማን ሕፃናት መርጃ ማዕከል (The Children's Heart Fund of Ethiopia) አበርክቷል።









ማኅበሩ ይህንን የጀመረውን አገልግሎት ለማጠናከር የባንኩ የማኔጅመንት አባላትና ሠራተኞች በአባልነት ተመዝግበው አስተዋጽኦዋቸውን እንዲያጠናክሩ ጥሪ አቅርቧል።

## የኢትዮጵያ ልማት ባንክ አ.ኤ.አ የ2022/23 የሁለተኛ ሩብ ዓመት የስራ አፈፃጸም

ብር በቢሊዮን

| የአፈጻጸም መለኪያዎች | 2022/23 | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | 2ኛው ሩብ ዓመት | | | 1ኛ ሩብ ዓመት | የአፈጻጸም ለውጥ በ% |
| | ዕቅድ | ክንውን | አፈጻጸም | ክንውን | |
| 1.1 የብድር ማጽደቅ/መፍቀድ | 8.56 | 7.75 | 90.49 | 4.57 | 69.49 |
| 1.2 የብድር መልቀቅ | 6.91 | 3.43 | 49.68 | 3.46 | (0.73) |
| 1.3 የብድር መሰብሰብ | 3.57 | 1.90 | 53.31 | 4.83 | (60.56) |
| 1.4 ጠቅላላ የብድር ክምችት | 69.37 | 66.23 | 95.48 | 63.29 | 4.64 |
| 1.5 የተበላሸ የብድር መጠን | 17.01 | 19.35 | 87.90 | 19.57 | (1.12) |
| 1.6 የተበላሸ የብድር ምጣኔ | 24.52% | 29.21% | 83.92 | 30.92% | (5.51) |
| 1.7 የተጣራ የትርፍ መጠን | 0.66 | 0.68 | 102.92 | 0.74 | (8.49) |

- ባንኩ በሁለተኛው ሩብ ዓመት ከደንበኞች ለሚቀርቡ እና የባንኩን የብድር መስፈርት የሚያሟሉ የብድር ጥያቄዎችን ተቀብሎ ለማጽደቅ ብር 8.56 ቢሊዮን ያቀደ ሲሆን ክንውኑም ብር 7.75 ቢሊዮን በማድረስ የዕቅዱን 90.5 በመቶ አፈጻጸም አስመዝግቧል ። ከባለፈው የሩብ ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸርም በ69.5 በመቶ ብልጫ አሳይቷል።
- ባንኩ በሁለተኛው ሩብ ዓመት ለደንበኞቹ ብድር ለመልቀቅ ብር 6.91 ቢሊዮን ያቀደ ሲሆን ክንውኑም ብር 3.43 ቢሊዮን በማድረስ የዕቅዱን 49.7 በመቶ አፈጻጸም አስመዝግቧል ። ከባለፈው የሩብ ዓመት ጋር ሲነጻጸርም በ0.7 በመቶ ቅናሽ አሳይቷል።
- በሁለተኛው ሩብ ዓመት ባንኩ ብር 3.57 ቢሊዮን ለመሰብሰብ ያቀደ ሲሆን ክንውኑም ብር 1.90 ቢሊዮን በማድረስ የዕቅዱን 53.3 በመቶ አፈጻጸም አስመዝግቧል ። ከባለፈው የሩብ ዓመት ጋር ሲነጻጸርም በ60.56 በመቶ ቀንሷል።
- በሁለተኛው ሩብ ዓመት የተበላሸ የብድር መጠንን ወደ ብር 17 ቢሊዮን ዝቅ ለማድረግ ያቀደ ሲሆን ክንውኑም ወደ ብር 19.34 ቢሊዮን የጨመረ ሲሆን ይህም የዕቅዱን 88 በመቶ አፈጻጸም አስመዝግቧል ። ከባለፈው የሩብ ዓመት ጋር ሲነጻጸርም በ1.1 በመቶ ቀንሷል።
- ባንኩ በሁለተኛው ሩብ ዓመት ከጠቅላላ የብድር ክምችት ውስጥ የተበላሸ የብድር ምጣኔውን ወደ 24.5 በመቶ ዝቅ ለማድረግ ያቀደ ሲሆን ክንውኑም 29.2 በመቶ ያደገ ሲሆን የዕቅዱን 84 በመቶ አፈጻጸም አስመዝግቧል ። ከባለፈው የሩብ ዓመት ጋር ሲነጻጸርም በ5.5 በመቶ ቀንሷል።
- ባንኩ በሁለተኛው ሩብ ዓመት ጠቅላላ የብድር ክምችት መጠኑን ብር 69.4 ቢሊዮን ለማድረስ ያቀደ ሲሆን ክንውኑም ብር 66.2 ቢሊዮን በማድረስ የዕቅዱን 95.5 በመቶ አፈጻጸም አስመዝግቧል። ከባለፈው የሩብ ዓመት ጋር ሲነጻጸርም በ4.6 በመቶ ጭማሪ አሳይቷል።

# የኢትዮጵያ ልማት ባንክ በአዲስ መልክ የተዋቀሩ ዓበይት እና ንኡሳን ቅርንጫፎች

| ተ.ቁ | የዲስትሪክት ስም | የቅርንጫፍ ስም |
|---|---|---|
| 1 | አዳማ ዲስትሪክት | አዳማ |
| | | ቢሾፍቱ |
| | | አሰላ |
| 2 | አርባ ምንጭ ዲስትሪክት | አርባ ምንጭ |
| | | ያቤሎ |
| | | ጂንካ |
| 3 | አሶሳ ዲስትሪክት | አሶሳ |
| | | መተከል |
| | | ነጆ |
| 4 | ባህር ዳር ዲስትሪክት | ባህር ዳር |
| | | እንጅባራ |
| | | ሞጣ |
| | | ቻግኒ |
| 5 | ቦንጋ ዲስትሪክት | ቦንጋ |
| | | ሚዛን |
| | | ቴፒ |
| 6 | ደብረ ብርሃን ዲስትሪክት | ደብረ ብርሃን |
| | | ሸዋሮቢት |
| | | አረርቲ |
| | | ሸዋ |
| 7 | ደብረ ማርቆስ ዲስትሪክት | ደብረ ማርቆስ |
| | | ቡሬ |
| | | ፍኖተሰላም |
| | | ደጀን |
| | | ቢቸና |
| 8 | ደሴ ዲስትሪክት | ደሴ |
| | | ሰቆጣ |
| | | ኮምቦልቻ |
| | | ወልዲያ |
| | | ከሚሴ |
| | | ላሊበላ |
| | | መካነሰላም |
| 9 | ድሬ ዳዋ ዲስትሪክት | ድሬ ዳዋ |
| | | ሐረር |
| | | ጭሮ |
| | | ገለምሶ |
| 10 | ጋምቤላ ዲስትሪክት | ጋምቤላ |
| | | መቱ |
| | | ጎሬ |
| 11 | ጎባ ዲስትሪክት | ጎባ |
| | | አዳባ |
| | | ጊኒር |
| 12 | ጎንደር ዲስትሪክት | ጎንደር |
| | | ደባርቅ |
| | | ደብረ ታቦር |
| | | እስቴ |
| | | ጋይንት |
| | | ገንደውሃ |
| 13 | ሀዋሳ ዲስትሪክት | ሀዋሳ |
| | | ዲላ |
| | | ይርጋለም |
| | | አለታወንዶ |
| | | ቡሌ ሆራ |
| | | አዶላ ወዩ |
| 14 | ሁመራ ዲስትሪክት | ሁመራ |
| | | ዳንሻ |
| 15 | ጅግጅጋ ዲስትሪክት | ጅግጅጋ |
| | | ጎዴ |
| | | ደገሃቡር |
| | | ቀብሪደሃር |
| 16 | ጂማ ዲስትሪክት | ጂማ |
| | | አጋሮ |
| | | በደሌ |
| 17 | መቀሌ ዲስትሪክት | መቀሌ |
| | | ሽሬ እንዳስላሴ |
| | | አዲግራት |
| | | አክሱም |
| | | አድዋ |
| | | አላማጣ |
| | | ውቅሮ |
| | | ማይጨው |
| | | አቢአዲ |
| 18 | ነቀምቴ ዲስትሪክት | ነቀምቴ |
| | | ደምቢዶሎ |
| | | ጊምቢ |
| | | ሻምቡ |
| | | ባኮ |
| 19 | ሰሜን ምስራቅ አዲስ አበባ ዲስትሪክት | ምስራቅ አዲስ አበባ |
| | | ሰሜን አዲስ አበባ |
| | | ፍቼ |
| 20 | ሰመራ ዲስትሪክት | ሰመራ |
| | | አሳይታ |
| | | አዋሽ 7 ኪሎ |
| 21 | ሻሸመኔ ዲስትሪክት | ሻሸመኔ |
| | | ባቱ |
| | | ሃላባ ቁሊቶ |
| 22 | ደቡብ ምዕራብ አዲስ አበባ ዲስትሪክት | ምዕራብ አዲስ አበባ |
| | | ደቡብ አዲስ አበባ |
| | | ሰበታ |
| | | አምቦ |
| | | ወሊሶ |
| | | ቡራዩ |
| | | ጊንጪ |
| 23 | ወላይታ ሶዶ ዲስትሪክት | ወላይታ ሶዶ |
| | | ሆሳዕና |
| | | ዱራሜ |
| | | ሳውላ |
| 24 | ወልቂጤ ዲስትሪክት | ወልቂጤ |
| | | ቡታጅራ |
| | | ወራቤ |